## ኢየሱስ ክርስቶስ አማላጅ ወይስ ተማላጅ?

ምልጃን በሚመለከት ርእሱ በጥያቄ ተነስቷል በመጠይቅ የተከፈተው ምክንያት ሰላለው ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በራሪ ጽሁፎች ከሌሎች ክፍሎች በተገኘው አጋጣሚና ስፍራ ሁሉ በኦርቶዶክስ ምእመናን እጅ እየገቡ ናቸው። ኦርቶዶክሳዊ ጽሑፎች አይደሉም በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሚታመነውን የአማላጅነት ቀኖና አንዳንድ ከሐዲስ ኪዳን የተለቀሙ ጥቅሶችን ርእሳቸውና ጎዳጋቸው ሳይገነዘብ በመውሰድ ለተቃውሞ የሚሰራጩ ጽሑፎች መኾናቸው በይዘታቸው ታውቋል።

ከምንጫቸውም እንጻር ብናያቸው የእኛ አይደሉም ሰለዚህ ነው ወደ ዝግጅት ክፍላችን መልስ እንድንሰጥባቸው ለሃይማኖታቸው ቁጭት ካላቸው ምዕመናን ዘንድ ጥያቄዎች በተከታታይ በየጊዜው የሚጐርፉልን ይኸን ጭብጥ ዋቢ አድርገን ምላሽ ለመሰጠት እንገደዳለን።የእኛ ዓላማ የሚያተኵረው የቤተ ክርስቲያናችንን እምነትና ሥርዓት ለምዕመናኖቻችን ግልጽና ነጻ በኾነ መልኩ ማቅረብ ማሳወቅ ማስተማር ሰለኾነ ወደ ጥቃቅን ክርክሮች ገብተን ከማስተማር ሂደታችን ወደ ሌላ አቅጣጫና የእንኪያ ሰላንቲያ መድረክ መክፈቱ የመንፈሳዊነቱን ለዛ ሰለ ሚያሳጣው በዚህ ጉዳይ ላይ አላተንኮርንም ነበር። ምርጫችንም አይደለም። ይሁን እንጂ አንዳንዴ አልፎ አልፎ ሁኔታዎች ሲያሰገድዱንና የእምነታችንን አቅጣጫ ይፋ በኾነ መልኩ የሚጋፋ ሲመጣ በአድር ብዬ ጠባይ ማለፉ ሕሊናችንንም ኾነ ዓላማችንን የሚነካ በመኾኑ ትኩረት መሰጠታችን አይቀርም። ሰለዚህ ነው ሾላ በድፍኑ «አማላጃችን ነውን?» በሚል መጠይቅ ለመነሳት የቃጣ ነው።

ይኸ ጥያቄ የመገረም ጥያቄ ይመሰላል። በከፊል የመገረም ምልክት ይታይበታል በሌላ መልኩ ግን ምልጃን በሚመለከት እንደ ዋና ጉዳይ ሆኖ በበራሪ ጽሑፎቹ የተወሳ ነጥብ ሰለኾነ የመጠይቁን እንብርት በማመልከት ትኩረት እንዲሰጥበት የሚያነቃቃ ዘይቤንም ያቀፈ መኾኑንም ያመለክታል።

ወደ ዋናው ፍሬ ነገር ስንገባ «አማላጃችን ነውን?» ሲባል በውስጡ ሌላ ጥያቄንም ዘግቦ ይገኛል ። ማን? ለማን? ወደ ማን? ወዘተ የተባሉት የጥያቄ ምልክቶች የሚወለዱት ከዚሁ ርእስ ውስጥ ነው እንደ እኛ እምነት ሳይኾን እንደ ተከራካሪዎቻችን አሰተሳሰብ ለመጠይቁ ምላሽ ለመሰጠት ብንሞክር ከቅዱስ መጽሐፍ ፅንስ ሐሳብ ውጭ የምሥጢር ሕፀፅ (ጉድለት) እንዳለው በግልጽ እናየዋለን። እንደ እነርሱማ አባባል ከአንድ በራሪ ጽሑፍ የተገኘ ነው። «አማላጃችን ማነው? » በሚል ርእስ ሥር የሚከተለው ሐተታ ተሰጥቶበታል።

«አማላጅ ማለት አንድን ሰው መክሎ የአንድን ሰው አቤቱታ ይዞ በሌላ ሰው ፊት ወይም በአምላክ ፊት የሚቀርብ ማለት ነው።» ሰው ሁልጊዜ  በአንድ በከበረ ሰው ፊት ለመቅረብ ብቁ የሆነ ካል መሰለው ወይም መብት ከሌለው በዚያ ሰው ፊት ማቅረብ የሚፈልገውን ጥያቄም ሆነ ልመና ይዞ በእርሱ ፋንታ የሚቆምለትን ሰው ይፈልጋል። ይህ አቀራረብ በአንድ በከበረ ሰው ፊት ለመቅረብ በምንፈልግበት ጊዜብቻ የሚቆምለትን ሰው ይፈልጋል። ይህ አቀራረብ በአንድ በከበረ ሰው ፊት ለመቅረብ በምንፈልግበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን በተለይ በእግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ በምንፈልግበት ጊዜ በኃጢአታችን ምክንያት ዘው ብለን በእግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ ሕሊናችን ሰለማይፈቅድልን በእግዚአብሔር ፊት ልመናችንንም ሆነ ሰዕለታችንን የሚያቀርብልን አማላጅ እንፈልጋለን። ከክርስቲያኖች ዋና መመሪያችን የእግዚአብሔር ቃል ሰለሆነ ሰለ ማማለድ ምን እንደሚል እንመልከት።

«አንድ እግዚአብሔር አለና በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፤ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስኢየሱስ ነው።» 1 ጢሞ2 ቁ5። ከዚህ ጥቅስ እንደምንመለከተው ኃጢአተኞች በሆንነው በእኛና ቅዱስ በሆነው በእግዚአብሔር መካከል ሆኖ እኛን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኘው እንደ እኛ ሰው ሆኖ ከድንግል ማርያም የተወለደው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ኢየሱስ ራሱየተናገረው ቃል ከዚህ ጋር አብሮ ይሄዳል «እኔ መንገድና እውነተኛ ሕይወትም ነኝ ከእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።» ዮሐ.14 ቁ 6። «በሩ እኔ ነኝ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል። ዮሐ.10፤ቁ 9።»

ከላይ የቀረበው ሐተታ ከተጠቀሱት መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ክርስቶስ አማላጃችን ነው አይልም በክርስቶስ አሰታራቂነትና በቅዱሳን አማላጅነት መካከል ያለውን ልዩነት ካለማወቅ የመነጨ ስሕተት ነው።

ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ሰው የሆነው እንደ ፍጡራን ሊያማልደን ሳይሆን በአዳም ኃጢአት ምክንያት የወደቀውን የሰው ዘር ከፅንስ ጀምሮ እስከ መስቀል ተጉዞ የሰውን ሁለንተናዊ ባሕርይ ከውድቀቱ ለማንሣትና ለማዳን ነው። ክርስቶስ እግዚአብሔርነት የሌለው ዕሩቅ ብእስ ይመስል አማላጃችን ነው አይባልም። በማዳን ሥራው ውስጥ ክርስቶስ ለሰዎች ያደረገውን ጸሎት ብቻ ነጥሎ ወስዶ አማላጃችን ነው ማለት ግድፈት ነው ከፅንስ ጀምሮ እስከ መስቀል ድረስ ያደረጋቸው ጉዞዎች ሁሉ ተጠቃለው የቤዛነት ሥራ ይባላሉ። ስለዚህ ክርስቶስ በሞቱ ደሙን አፍሶ ሥጋውን ቆርሶ ከባሕርይ አባቱ ከአብ፤ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ከራሱም ጋር በሞቱ ታረቀን፤ ከእግዚአብሔርነቱ ጋር አስታረቀን፤ ወይም ቤዛ ሆነን ካሰልንይባላል እንጅ እንደ ፍጡራን አማላጆች አማላጃችን አይባልም። አለመባሉንም አንድ በአንድ ለማሰረዳት እንሞክራለን። ከዚህ በፊት ስለአማላጅነት በመጽሔታችን እንደጠቀስነው ምልጃ ሦስት ሁኔታዎችን እንደ ሚያጠቃልል አውስተን ነበር። ይኸውም በአማላጅነት ውስጥ የምንመለከታቸው ነገሮች

ሀ)- የሚማለድለት (የሚማልዱለት)
ለ)- የሚማልድ (አማላጅ)
ሐ)- ምልጃን ተቀብሎ ምሕረቱን የሚያድል ተማላጅ

እነዚህ ነገሮች የቅዱሳንን አማላጅነት በጠቀስንበት ጊዜ ያየናቸው ሁኔታዎች ናቸው። ምልጃን ጠያቂው የሚማለድለት ሰው በእግዚአብሔር መሐሪነት (አዳኝነት) በቅዱሳን ምልጃ የሚያምን ነው። ቅዱሳን በቀደመ ልመናቸው እንዲያማልዱት በጸሎታቸው ይታመናል። በትሕትና ይጠይቃል። የሚማለድለት ስለእርሱ ይቅርታን ከእግዚአብሔር የሚጠይቁለት ቅዱሳን ናቸው። በሃይማኖትና በምግባር ፍጹማን ስለኾኑ ከፍጹምነት ላልደረሰው ደካማው ሰው በተሰጣቸው ጸጋና ቃል ኪዳን ይለምኑለታል። ስለዚህ አማላጆች ይባላሉ። የቅዱሳንን ጸሎት የምዕመኑን ትሕታና ተመልክቶ ይቅር የሚል ምሕረቱን የሚያድል ተማላጁ (ምልጃን ተቀባዩ) ሁሉን ማድረግ የሚችለው እግዚአብሔር ነው። ይኸ የፈጣሪ ሥራ ነው። ስለዚህ ክርስቶስን አማላጅ ካደረግነው ወይም ካልነው ከዚህ ምስጢር ዳኅፅ (ስሕተት) ውስጥ መውደቃችን ነው። ክርስቶስ ምንም እኛን ለማዳን ከኃጢአት ብቻ በቀር እኛ ልንሠራቸው የሚገባንን ትሩፋት ኹሉ ቢሠራ ለካስ ለአብነት ለአጽድቆተ ትስብእትና ለአቅርቦተ ሰይጣን (ሰይጣንን በትሕትና ሥራው አቅርቦ ሊፈርድበት ሥልጣኑን ሊገፈው) ነው እንጂ ተለማኙ ምልጃን ተቀባዩ ጌታ አስታራቂያችን (ቤዛችን) መባል ሲገባው ፍጡር ይመስል አማላጃችን አይባልም። ለዚሁም በቂ ማሰረጃ አለን። ሁሉንም በዚች አነስተኛ ጽሑፍ ማጠቃለል ባይቻልም አልፎ አልፎ ጠቅለል ባለ መልኩ መተንተኑ ይመረጣል።

ሀ) **«እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ ስለ ዓመጸኞችም ማለደ።»** (ኢሳ 53 ቁ 12)። ይህ ትንቢት ክርስቶስ ኃጢአት ሳይኖርበት ንጹሐ ባሕርይ ሆኖ ሳለ በሰው ዘር ኃጢአት ምክንያት በመሰቀል ላይ ተሰቅሎ ስለ ሰው መከራን ገንዘቡ በማድረግ ማዳኑን የሚያመለክት ትንቢታዊ ቃል ነው። ሙሉን ምዕራፍ ብንመለከተው ዝርዝር ሁኔታውን ያሰጨብጠናል። «ሰለ ዓመጸኞችም ማለደ» የሚለውን ሐረግ ይዘው «ማለደ»ከተባለ አማላጅ የማይባልበት ሰበቡ ምንድነው ቢባል ምልጃ ከቤዛነት ሥራው አንድ ንዑስ ክፍል ነው። ጠቅላላ የማዳን ሥራውን አያጠቃልልም። ቤዛነቱን በመሰቀል እስከ ፈጽም ድረስ ለሰው ሁሉ አብነት (መምህርም) ሆኖ የትሩፋትን ጎዳና ቀይሷል።

በሔደባቸውም የትሩፋት ጐዳናዎች ተከታዩቹ እንዲጓዙ መክራል አርአያ ሆኗል። የእርሱን ፈለግ ተከትለው የተሩፋት ተጋድሎ ያደረጉ ቅዱሳን ወዳጆቹ አያሌ ናቸው። ኢሳይያስ «ሰለ ዓመጸኞክ ማለደ» ሲል በነብዩ ዘመን ክርስቶስ እንደ ማለደ አድርጐ በኃላፊ ግስ ተጠቅሞአል። ይኸ የመጸሕፍት አካሄድ ነው መጻሕፍት ምሥጢር እንጂ ዘይቤ አይጠነቅቁም ተብሎ የሚነገር የትርጓሜ ዐዋጅ አለ።

በዕብራውያን ምዕ 7 ቁ25 ። **«ስለ እነርሱም ሊማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና»** ተብሎ የተጠቀሰውም ካሳ በመሰቀል ላይ ከተፈጸመ በኋላ ለወደፊት እንደሚያማልድ አድርጐ በትንቢት አንቀጽ መናገሩ የመጻሕፍት አካሄድ በመኾኑ ነው እንጂ ድርጊቱስ በዕለተ ዓርብ ተፈጽሟል።

ድኅነተ ዓለም በመሰቀል ላይ መፈጸሙን ራሱ ባለቤቱ ጌታችን ሰለ መሰከረ ሌላ አሰረጅ ከፈጣሪ ቃል በላይ አንፈልግም (ዮሐ19 ቁ30።) ጌታችን «ተፈጸመ» ማለቱ ነቢያት ሁሉ ሰለ ድኅነተ ዓለም የተናገሩት የቤዛነት ተግባር ፍጻሜውን አገኘ ማለቱ ሰለሆነ ፍጡርይመስል እንደ አንዳንዶቹ አስተሳሰብ አባቱን ዘወትር ማርልኝ እያለ ደጅ የሚጠና አማላጅ አለመኾኑን ማሰተዋል ይገባል።

የሐዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት እንደ መኾኑ መድኃኒታችን የጸሎተ ሐሙስ የስቅለት ዋዜማ ሥርዓተ ቁርባንን ከፈጸመ በኋላ የአሰታራቂነቱን የምልጃ ጸሎት አቅርቧል። (ዮሐ 17፤1-26) በመጨረሻም ነቢዩ ኢሳይያስ በትንቢቱ እንዳመለከተው በዕለተ ዓርብ በመሰቀል ላይ ሳለ ካቀረባቸው ጸሎቶች ሁለቱን እናያለን።

ሀ)- «ጌታ ኢየሱስም አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁትመና ይቅር በላቸው አለ»
ለ) «ኢየሱስም በታላቅ ድምጽ ጮኸ፡- አባት ሆይ ነፍሴን በእጅግ አደራ እሰጣለሁ አለ» (ሉቃ 23 ቁ3 4ና46)።

በዚህ አነጋገሩ ተሰናክለው ከአምላክነት ውጭ አድርገው ክርስቶስን እንደ አንድ ጻድቅ ወይም ነቢይ በመገመት የእነ አብርሃም የነሙሴ ጓደኛ ሊያደርጉት የሚቃጣቸው ይኖራሉ። ምሥጢሩ ስላልገባ ቸው በንባብን ተሰናክለው ነው እንጂ መጽሐፍ ቅዱሱስ ለጥርጥራቸው በር ከፋች አይደለም።

ኢሳይያስ እንደ ተነበየው ክርስቶስ ያደረጋቸው የትሕትና ስራዎች ሁሉ ስለ እኛ ድኅነት የሚያ በስሩ እንጂ ክርስቶስ ከባሕርይ አባቱ ከአብ በባሕርይ የተለየ በማእረግ (በክብር) አንሶ ራሱ መፈጸም የ ማይችል ሆኖአይደለም። ይኸንንማ እንዳንል ከአባቱ ከአብ ጋር በክብር ትክክል ነው። በመልክ ይመስለ ዋል በባሕርይም ይተካከለዋል። አባቱ የሚሠራውን ከአባቱ ሳይለይ ይሠራል። የአባቱ ገንዘብ ሁሉ ገንዘ ቡ ነውጸሎትን ተቀብሎምሕረትን ማደል እንደ አባቱ ገንዘቡ ነውና ከፍጡራን ጋር አይነጻጸርም። ይኸ በምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርት ክርስቶስ ሰለ ድኅነተ ዓለም ወዶ ፈቅዶ ያደረገው አትሕቶ ርእስ (ራስን ዝ ቅ ማድረግ) ይባላል ዝርዝር ሐተታው በምሥጢረ ተዋሕዶ የሚገለጽ እንጂ በዚህችቊንጽል ጽሑፍ ተቀ ንጭቦ የሚቀርብ ሰላልሆነ ለጊዜው ዓይነታውን አመልክተን ማለፉን መርጠናል።(ዮሐ 1፣1-3 ዮሐ 1፣14 ዮሐ 5 ቁ17-18 ዮሐ 17፣15 ዮሐ 17፣10)።ክርስቶስ ወዶ ፈቅዶ ራሱን በማዋረድ ተዋርደን የነበርን እኛ ከብረናል። ባለጸጋው እሱ ድሀ ሆኖ በመገለጹ ድሆች የሆን እኛ በእርሱ ትሕትና በልጽገናል። ይኸውም በማዳን ሥራው ፍጹም ጽድቅ ድኅንነት ተጐናጽፈናል። (1ኛ ቆሮ 8 ቁ 9።)

ከላይ ክርስቶስ ጸሎት ማቅረቡ የሐዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት እንደ መሆኑ ነው። ያልነውን ከዚህ ላይ ማጤን ይገባናል። ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ በተደጋጋሚ እንዳሰገነዘበን የክርስቶስ ሊቀ ካህናትነት ከኦሪታዊው ሊቀ ካህናት ልዩነትም ብልጫም እንዳለው በእንጻራዊ አንድምታው በሰፊው ያብራራልንን ማሰተዋል አለብን። (ዕብ 6፤11-28 ዕብ 9፤7-14)።

የኦሪቱ ሊቀ ካህናት ፍጡር ኃጢአተኛ ሚች ሰለሆነ ሰለ ራሱና ሰለሌሎችም ባዕድ መሥዋዕት የእንሰሳት ደም ያቀርባል። በዓመት አንድ ጊዜ በቅድስተ ቅዱሳን መሥዋዕት ያሳርጋል። በዚህ መሥዋዕ ት አፍአዊ ኃጢአት ይነጻበታል እንጂ ፍጹም ድኅነትን ሊያሰገኝ አልቻለም ክርስቶስ ግን ከቅድስት ድን ግል ማርያም ሰው ሆኖ ራሱ ካህን መሥዋዕት አቅራቢ ባዕድ መሥዋዕት ሳይሆን ራሱን ሰውቶ ሥጋውን ደሙን በመሰቀል ፈትቶ አሰታራቂም ተወካፌ መሥዋዕትም (መሥዋዕት ተቀባይም) ሆኖ አንድ ጊዜ በእ ለተ ዓርብ በፈጸመው ካሣ ዓለምን ሁሉ ሲያድን ይኖራል እንጂ እንደ ኦሪታውያን ካህናት ዕለት ዕለት ወይም በየዓመቱ መሥዋዕት ማቅረብ አላሰፈለገውም። እነርሱ ፍጡራን እሱ ፈጣሪ እነርሱ ኃጢአተኞች እርሱ ግን ንጹሐ ባሕርይ፤ እነርሱ ሚቾች እርሱ ግን ዘላለማዊ ሕያው ባሕርይ የእነርሱ መሥዋዕት ባ ዕድ የእንሰሳት የእርሱ ግን የራሱ ባሕርይ ሥጋውና ደሙ ነውና።

ሰለዚህ ልዩነቱ የትየለሌ ነው እንደ ሰማይና ምድር ከዚያም በላይ የተራራቀ ነው እስከ ክርስቶ ስ የነበረው ዘመን ዓመተ ፍዳ ዓመተ ኵነኔ መባሉ በኦሪት ፍጹም ድኅነት ስላልተደረገበት ነው ፍጹም ድኅነት የተገኘውበክርስቶስ ሰው መሆንና በፈጸመው ካሣ የማስታረቅ ሥራው ሰለሆነ ወንጌል የድኅነታች ን ምንጭ ሆናለች። የቀድሞውን ዘመን ዓመተ ፍዳ ዓመተ ኵነኔ በማሰመልከተ ነቢያት ኩሉ ተባብረው ምሬታቸውን ገልጸዋል። (ኢሳ 64፣6 መዝ 13፣14 1-3) በክርስቶስ ቤዛነት ግን በእርሱ ካሣ በአዳም ኃጢ አት ምክንያት ሲማረር የነበረው የሰው ዘር አምኖ ከታዘዘ ጽድቅ ጸጋ ተትረፍርፎ እንደተሰጠው በማረጋ ገጥ ቅዱስ ጳውሎስ ያበሰራል። (ሮሜ ምዕ 5 ቁ -21)

እንግዲህ የክርስቶስ ሥራውና ካሣ (ማስታረቅ) መሆኑን ከዚህ በላይ በገለጽነው መሠረት ካሳየን ዘንድ ወደ ጥንተ ነገራችን ተመልሰንከላይ የተጠቀሱትን ጥቅሶች እንመርምራቸው።

በሉቃስ ወንጌል 23 ቁ 34 ና47 የተመለከትናቸው ኃያለ ቃሎች ምስጢራቸውን ላልመረመረ ሰው ያሰነካክላሉ ብለን ነበር። ከተመረመሩ ግን በዓመተ ፍዳ በዓመተ ኵነኔ፡- በዘመነ ኦሪት ጸሎቱ የማይሰ ማ መሥዋዕቱ ጉዳይ የማይፈጽም የነበረው የሰው ድካም በክርስቶስ የማስታረቅ አገልግሎት ሳቢያ ኃይል አግኝቶ ጸሎቱ ተሰሚ መሥዋዕቱ ጉዳይ ፈጻሚ ሆኖለት እንደ ኦሪት ዘመን ምልጃው በሥጋ ክልል ተወ ሰኖ የሚቀር ብቻ ሳይሆን ነፍስን ጭምር ጸጋን በማጐናጸፍ ከውድቀት ለማዳን የሚያበቃ ሆኖ መገኘቱን የሚያረጋግጡልን ኃይለ ቃሎች መሆናቸውን በውል ስናሰተውላቸው ለመገንዘብ እንችላለን።

መድኃኒታችን ለሁሉ ነገር መሪያችንም አሰተማሪያችንም እንደመሆኑ አርአያውን እንድንከተል አብነት እንድናደርገው «ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ (ወንጌልን መሰቀልን) ከእኔም ተማሩ (አብነት አድ

ርጉኝ በግብር ምሰሉኝ) እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና (ለጠላቶቹ መጸለይ ተበድሎ መካስ) ለነፍሳችሁም እረፍት ታገኛላችሁ» (ማቴ 11 ቁ. 29) ብሎ በቃል አስተምሮአል። በተጨማሪም በማንኛውም ነገር እርሱን አምነው አርአያውን በመከተል እርሱ የሠራቸውን የድኀነት ስራዎች አሰመሰለው የሚሰሩ የግብር ተከታዮች እንዳሉት ሲያስረዳ እንዲህ ብሏል። **«እውነት እውነት እላችሃለሁ በእኔ ዘንድ የሚያምን እኔ የማደርገውን *ሥራ* እርሱ ደግሞ *ያደርጋል* ከዚህም የሚበልጥ *ያደርጋል*።»** (ዮሐ. 14 ቁ.12)

ክርስቶስን አብነት አድርገው የሠሩ ቅዱሳን ከሐዋርያት ዘመን አንሥቶ ብዙዎች ናቸው። ከብዙዎቹም መካከል የዲያቆናት አለቃ ቀዳሚ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ ክርስቶስን መሰሎ የሠራውን ተግባር ማጤኑ ብቻ ልብላለው ሰው ሊያስረዳ ይችላል። ቅዱስ እስጢፋኖስ የመጨረሻውን የሰማዕትነት ጽዋውን ሰለ ክርስቶስ በውግረት ሲቀበል በተናገራቸው ኃይለ ቃላት ክርስቶስን አብነት ከማድረጉም በላይ የክርስቶስ ክብር ከአብ ጋር አሰተካክሎ የሚያሳየን ሆኖ ይገኛል። ይኸውም ክርስቶስ እንደ ባሕርይ አባቱ እንደ አብ ጌትነት ያለው የቅዱሳንን ነፍስ የሚቀበል ሰለራሳቸው የሚለምኑትን ልመና ስለሌሎችም የሚሰማ ሰምቶም ምሕረትን የሚያድል ይቅር ባይ አምላክ መሆኑን እንደ አብ በአብ ሕልውናም በጌትነት ዙፋን ላይ የሚኖር የባሕርይ ንጉስ ስግደት አምልኮት የሚቀርብለት ጌታ መሆኑን ይመሰክርልናል። በግብረ ሐዋርያት ምዕ 7፤59-60 የተጠቀሰውን ከሉቃስ ጋር አነጻጽረን ምሥጢሩን እንገንዘብ።

ቀደም ብሎ አንደተገለጸው ጌታችን የትሕትና *ሥራ* የሠራው ለአብነት ለካሳ ሲሆን ጊዜውም ከፅንሰ እስከ ትንሣኤ ባለው ጊዜ ውስጥ ነው። ሰው ከመሆኑ አሰቀድሞም ሆነ ከትንሣኤው በኋላ መማለድ እንጂ ማማለድ የለበትም ስለዚህ መድኃኒታችን ቤዛነት አሰታራቂያችን እየተባለ ይመሰገናል።

ለቅዱሳን ሐዋርያትና ለመሰሎቻቸው ሁሉ አብን በተሰቀለው በተቸነከረው ልጅህ ብለው ቢለምኑት ወይም ራሱን ክርስቶስን የተሰቀልከው የተቸነከርከው ጌታ ሆይ ብለው ሰሙን ጠርተው ቢለምኑት ጸሎታቸውን ተቀብሎ እንደሚፈጽም በሮሜ 8 ቁ 34 **ላይ ያለውን ይዘው «አማላጃችን ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው» በማለት የሚፋለሙን እንደነርሱማ ትርጓሜ ከሄድን አማላጅ የሚባለው ጌታ ኢየሱስ ብቻ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስም አማላጅ መባሉ ነው። ምክንያቱም በሮሜ ምዕ** 8 **ቁ**26 **ና** 27 **«መንፈስ ራሱ ይማልድልናል..... ሰለ ቅዱሳን ይማልዳልና»** ከሚል መንፈስ ቅዱስም እንደ ክርስቶስ አማላጅ ሊሆን ነው። እንግዲህ እንደ ሮሜ 8 አነጋገር አንድ አማላጅ ብቻ ሳይሆን ሁለት አማላጆች ሊኖሩን ነው። መንፈስ ቅዱስም አማላጅ ከተባለ ጌታ ኢየሱስን ብቻ አማላጃችን ነው ለምን አሉ? እኛስ አይደንቀንም ለእነርሱ ግራ ይግባቸው እንጂ ግእዛችንም አማርያችንም የተሰተካከለ ንባብ ሰለሆነ አይምታታብም። ቀጥተኛውን ንባብ እስቲ እንመልከትና የሕሊና ዳኝነት እንስጥበት። «በመንፈስ ቅዱስም ከድካማችን ይረዳናል፤ እንግዲያማ ተሰፋችንን ካለወቅን ጸሎታችን ምንድነው፤ ነገር ግን እርሱ ራሱ መንፈስ ቅዱስ ሰለ መከራችን ሰለ ችግራችን ይመልሰልናል። እርሱ ልቡናችንን ይመረምራል፤ ልብ ያሰበውንም እርሱ ያውቃል ሰለ ቅዱሳንም ይፈርዳል በእግዚአብሔር ዘንድ ያማልዳል የሚል ንባብ የለም ስህተቱን እያረሙ ያንብቡ።

__ክርስቶስ አማላጅ ለመኾኑ እንደ ሰነድ ያቀረቡትም ዮሐ 10 ቁ 9 ና ዮሐ 14 ቁ 6 ጥቅሶች ሲመረመሩ ንባባቸውም ሆነ ትርጓሜያቸው አማላጅ አያደርጉትም እንዲያውም የምልጃን ነገር የሚያነሳ አንዳችም ቃል አይገኝባቸውም።__

1ኛ/ በዮሐ. 1 ቁ 9 የተጠቀሰው «በሩ እኔ ነኝ የሚገባ ቢኖር ይድናል» አለ አንጂ አማላጅ እኔ ነኝ አላለም። በግእዙ ወንጌል «እነውእቱ አንቀጸ አባግዕ ዘበአማን ዘአቦ ብእሲ እንተ ኀቤየ ይድኀን ወይበውእ ወይ መጽእ ወይረክስ ምርአየ።» ይላል ቃል በቃል ሲተረጐም ወይም ነጠላ ትርጓሜው እንደሚከተለው ይነበባል። «እውነተኛ የበጎች በር እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የገባ ሰው ይድናል፤ ይገባል ይወጣል መሰማርያም ያገኛል» ንባቡ የሃይማኖት አንቀጽ ነው። በክርስቶስ በማመን ሰለሚገኘው ጸጋ በምሳሌያዊ አነገጋገር የሚያሰረዳ ነው አንጂ ክርስቶስን አማላጃችን ነው አይለውም። ኦርቶዶክሳዊ ትርጓሜውን እንደሚከተለው እናያለን። በምሥጢር የሚገናዘቡ ሦስት አወራረድ አሉት\ሦስቱንም በቅደም ተከተል እንመልከታቸው።

ሀ) ወደ ቤት ለመግባት በደጅ (በበር) መግባት እንደሚያሰፈልግ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመንግባት በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ ልጅነት የባሕርይ አምላክነት አምኖ መጠመቅ ያሰፈልጋል። ሳያምኑበት መዳን አይቻልምና። (ዮሐ. 7፤47 የሐዋ *ሥራ* 8፤36-39 1ኛ ዮሐ 2 ቁ 20-21) የበጎች ደጅ ክርስቶስ ነው በጎቹ ምእመናን ናቸው። ወደ እኔ የገባ ሰው ይድናል ማለቱ በእኔ አምላክነት ያመነ ሰው ከክህደት ይድናል ሲል ነው። ይገባል ይወጣል መሰማሪያም ያገኛል ሲልም ወደ ሃይማኖት ይገባል በጎ *ሥራ* ለመስራት ይወጣል ሰለ ሃይማኖቱም እሳቱን ሰለቱን መስቀሉን ማለት ሰማዕትተትን ያገኛል ሰለ ስሜ ይመሰክራል ማለቱ ነው።

ለ) ሁለተኛውም ትርጓሜ እኔን አብነት ያደረገ ከፍዳ ከኩነኔ ገሃነም ይድናል። ወደ ወንጌል ይገባል ማለትም በወንጌል ያምናል ለማሰተማር ይወጣል። ጉባዔን ምእመናንን ያገኛል ሲል ነው (1ኛ ዮሐ 2 ፤3-6) ።

ሐ) ሦስተኛው ትርጓሜ እኔን በኩር ያደረገ ከፍዳ ከኩነኔ ይድናል። ከፈቃደ ሥጋ ይወጣል። ወደ ፈቃደ ነፍስ ይገባል ክብረ ሥጋ ክብረ ነፍስን ያገኛል መንግሥተ ሰማይን ይወርሳል ማለት ነው። (ገላ ምዕ.5፤16-26)።

2ኛ (በየሐ 14 ቁ 6) ተጠቀሰውም የሃይማኖት አንቀጽ ነው እንጂ ክርስቶስ አማላጅ ነው የሚል አይደለም። በዚሁ ምዕራፍ ቁ 1ን ብንመለከት አርእስቱ በሃይማኖት ላይ ይመሠረትና እምነትን መሠረት አድርጎ ይነሣል። ቁ 5 ላይ የመንግሥተ ሰማያትን ጎዳና (መንገዱን) ታውቃላችሁ ቢላቸው መንገዱን እንዴት እናውቃለን ብለው መንገዱ በክርስቶስ ማመን መሆኑን ማለትም ሃይመኖት ወንጌል መሆኑን ስላልተረዱ በቁጥር 6 ላይ ወደ አብ የምወሰድ መንገድ እኔ ነኝ ይላቸዋል። አማላጅ ነኝ አላላም። ዝቅ ብሎ በጎዳት በቁ 7 ላይ «እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር። ከአሁን ጀምራችሁ ታውቁታላችሁ አይታችሁትማል» በማለት መንገድ ያለውን የሃይማኖት እውቀት መሆኑን ተርጉሞ ወልድን በሃይማኖት ማወቅ አብንም በሃይማኖት ማወቅ ወይም ማየት መሆኑን ያሰረዳቸዋል። ከቁጥር 8 እስከ 11። አብ በወልድ ወልድም በአብ ህልው መሆኑን ዘርዝሮ ከላይ በአርእስቱ ያነሳውን የሃይማኖት ነገር በጎዳት አጉልቶ በማሳየት ይደመድማል። እንግዲህ ምኑ ላይ ነው ክርስቶስ አማላጃችን ነው የሚያሰኘው ከመጽሐፍ የሌለ ፈጠራ እየወለዱ ተሳስቶ ማሳሳት አግባብ አይደለም። ኦርቶዶክሳዊ ትርጉሙንም ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን። በማሰተዋል ለመገንዘብ እንሞክር የጥበባት ባለቤት ምሥጢሩን ይግለጽልን አሜን።

እንደ ከዚህ በፊቱ ዮሐ 14 ቁ 17- በምሥጢር የሚገናዘብ ሦስት የትርጉም አወራረድ የአንድምታ ዘይቤ አለው።

የግዕዙ ንባብ ነጠላው እንደሚከተለው ይነበባል። «ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ አነ ውእቱ ፍኖተ ጽድቅ ወሕይወት ወአልቦ ዘይመጽእ ኀበ አብ ዘእንበለ እንተ ኀቤየ እምከመ ኪያየ አእመርክሙኒ እምአእመርክዎ ለአቡየኒ።» በአማርኛ ነጠላ ትርጉሙም እነሆ «የሕይወትና የጽድቅም መንገድ እኔ ነኝ ያለእኔ ወደ አብ የሚመጣ የለም። እኔን አወቃችሁኝ ቢሆን አባቴን ባወቃችሁት ነበር።

ሀ) የመጀመሪያ ምሥጢራዊ ትርጉሙ «የአንድነት የሦስትነት ባለቤት እኔ ነኝ ማለት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ብሎ ለማመን እኔን ማመን ያሰፈልጋል ማለት ነው። ምስጢረ ሥላሴ ጎልቶ የተነገረው ምሥጢር ሥጋዊ ሰው የሆነው ወልድ ከድንግል ሰው ከሆነ በኃላ ነው ከዚያ በፊት አልፎ አልፎ ለአንዳንድ ቅዱሳን እንደ አብርሃም ኢሳይያስ ላሉት ቢገለጽላቸው እንጂ እንደ ዘመነ ሐዲሱ ምሥጢረ ሥላሴ አለመከሰቱን የሚያመለክት ነው። እኔን ተወላዲ ካላለ አብን ወላዲ የሚለው የለም አብ ማለት አባት ማለት ነው። የማን አባት ቢሉ የወልድ የባሕርይ አባት ወልድ ማለት ልጅ ማለት ነው የማን ልጅ የአብ የባሕርይ ልጅ። የወልድን ልጅነት የማያምን የአብን አባትነት አያምንም ማለት ነው። በአብ ወላዲነት ለማመን የወልድን ተወላዲነት መቀበል ያሰፈልጋል። (ማቴ.11፤27 ዮሐ 1፤14 ና 18 2ኛ ዮሐ 1 ቁ 9-11 ማቴ 28፤19)። እኔንስ ተወላዲ ብላችሁኝ ቢሆንስ አባቴም ወላዲ ባላችሁት ነበር።

ለ) ሁለተኛው አወራረድ፡- «የትሩፋት ሥጋ የትሩፋት ነፍስ አብነት እኔ ነኝ። እኔን አብነት ካላደረጉ አባቴን ሥራ አሠራኝ የሚለው የለም። እኔንስ አብነት አድርጋችሁኝ ቢሆን አባቴንም ሥራ አሠራን ባላችሁትም ነበር። (ዮሐ. 13፤ 12-12 ዮሐ 15፤ 5-7)

ሐ) ሦስተኛው አወራረድ ደግሞ፡- «የከበረ ሥጋ የከበረ ነፍስ ባለቤት እኔ ነኝ። እኔን በኩር ካላደረገ አባቴን አክብረኝ የሚለው የለም። እኔን በኩር አድርጋችሁኝስ ቢሆን አባቴንም አክብረን ባላችሁት ነበር፤» ይላል። እንዲህ በዚያም ተባለ በዚህ የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት አብነት በኩርነት የሚያሳይ አነጋገር እንጂ የአማላጅነት ነገር አያነሣም።

በ1ኛ ዮሐ.2 ቁ 1 ላይ የተጠቀሰውን ይዘው ክርስቶስ ጠበቃችን ነው ሰለሚል ጠበቃ ማለቱ አማላጅ ማለት አይደለምን ይሉናል። የግዕዙም ሆነ አማርኛው ንባብ እንዲህ አይደለም አሁንም ንባቡን በትክክል እንመልከት። «ደቂቅየ ዘንተ እጽሕፍ ለክሙ ከመ ኢተአብሱ ወእመኒ ዘአንበበ ጵራቅሊጦስ ብነ ኀበ አብ ኢየሱስ ክርስቶስ ጻድቅ ውእቱ ይኀድግ ለነ ኃጣውኢነ።» ነጠላ ትርጉሙም «ልጆቼ እንዳትበድሉ ይህን እጽፍላችኋለሁ፤ የበደለም ቢኖር ጵራቅሊጦስ አለን ከአባት ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ቸር ነው። ኃጢአታችንን ያሰተሰርይልን ዘንድ» ይላል። ጵራቅሊጦስ በጽርዕ ቋንቋ ፓራክሊቶስ ማለት ነው። በዕብራይስጥ ደግሞ ፐራቅሊጥ ይባላል። አሰታራቂ አፍ ጠበቃ ትርጉሙን እያጣፈጠ የሚናገር ካፋማር ጠብ የሚል ትርጉም አለው። ዋናው ፍች ግን ጰራቅሊጦስ ማለት መሰተሥርዪ መጽንኢ መንጽሒ መሰተፍሥሒ ናዛዚ ከሣቲ ማለት ነው። ይቅር የሚል የሚያጸና የሚያነጻ ደስ የሚያሰኝ የሚያረጋጋ (የሚያጽናና አጽናኝ) ገላጭ (ምሥጢርን የሚገልጽ) ማለት ነው። ሰለ ጵራቅሊጦስ የተናገረውን ዘወር አድርጎ ክርስቶስን ጠበቃ (አማላጅ) ለማለት ከንባቡ መንፈስ ውጭ ለማተት መቃጣት ጥፋት ነው። መታረም ይገባዋል። የንባቡን መንፈስ (ትንጉሙ) «በድሎ ንስሐ የገባ ሰው ቢኖር ኃጢአታችንን የሚያስተሥርይልን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ዘንድ የሚሰድልን ጵራቅሊጦስ አለን። ኃጢአታችንን ያሰተሠርይልን ዘንድ ቸር የባሕርይ አምላክ ነው» የሚል ነው። (ዮሐ.14 ቁ15-17 ዮሐ.14፤ 25-26 ዮሐ 16 ቁ 7-15)።

የሐዋ. ሥራ 4 ቁ 12 ከሰው ወገን የማንም ስም አዳኝ (መድኃኒት) አለመሆኑን ይገልጻል። መድኃኒት መባል ማዳን ለወልድ እግዚአብሔር የተሰጠ የተዋሕዶ ስሙ ነው። በስሙ ይድኑታል። ኢየሱስ ማለት መድኃኒት ማለት ነው።

የተዋሕዶ ስም ማለትም ቃል ሥጋ ከሆነ በኋላ ማለትም ወልድ ከድንግል ሥጋንና ነፍስን ተዋሕዶ ሰው ከሆነ በኋላ የሰውነቱም የመለኮቱም ስም ነው። በሐዋ. ሥራ 4 ቁ 12 የተጠቀሰው ኃይለ ቃል ከማቴ. 1 ቁ 21 ና ሉቃ 1 ቁ 31 ጋር አንድ ነው። ቅዱስ ጴጥሮስ በሐዋ. ሥራ 3፤6 በተገለጸው መሠረት ሽባውን ያዳነው መድኃኒት በተባለ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው። አይሁድ በክርስቶስ ሰለማያምኑ በተቃወማቸው ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ ሽባውን ያዳኑት የዕሩቅ ብእሲ ስም ጠርተው አይደለም። አዳኝ ስሙን ጠርተው ነው ያዳኑት። ሰለዚህ የሚያድነውን እንደ እናንተ አንክደውም ብለው የባሕርይ አምላክ በተዋሕዶ የከበረ መሆኑን ለማሰረዳት የተናገሩት የምስክርነት ቃል ነው እንጂ ኢየሱስ ክርስቶስ አማላጃችን ነው ሲሉ የጠቀሱት ቃል አይደለም። የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት ለማሰረዳት መሆኑንም ለማወቅ ከዚህ ጋር የሐዋ. ሥራ ምዕ. 2 ቁ21 ና ኢዮኤ. 2፤32ን ከሮሜ ምዕ.10 ቁ. 8-13 ጋር በማገናዘብ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያድን ጌታ እግዚአብሔር መባሉን እንረዳ። እንግዲያውስ ራሱ እግዚአብሔር ከሆነ በሕልውና ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተገናዝቦ የሚመለክ የሚያድን መሆኑን ሲያስረዱን የባሕርይ ክብሩን ሲገልጹልን የተናገሩትን የሐዋርያትን ቃል ወደ አልሆነ አቅጣጫ አጠማዞ ለመተርጐም መቃጣት መሳሳት ነው። እንዳንሳሳት በትምህርተ ሐዋርያት ለመጽናት ያብቃን በተዋሕዶ የከበረው ኢየሱስ ክርስቶስ ከአባቱ ሳይለይ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ለዘላለም የተመሰገነ ነውና ቤዛነቱን አምነን ወዳጆቹን አክብረን ለመኖር በድንግል እናቱ ምልጃ ይታረቀን። አሜን (2ኛ ጴጥ. 3፤ 12-18)

**መለከት ከሚለው ሰኔ 1995 ከታተመው መጽሔት ሲራክ ገብረ ክርስቶስ ከጻፉት የተወሰደ።**